# አንድ - ቀን



Niguss
Digital Library

ከክፍሌ አቡቸር (ሻምበል)

# አንድ ቀን

ከክፍሌ አቡቸር (ሻምበል)

አዲስ አበባ (1982)

# ምስጋና

ለጥርቴ መሳካት ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ ለኢትዮጵያ መጻሕፍት አሣታሚ ድርጅትና ለአቶ ሁሴን ኑሩ፡-

ለሕትመቱ ጥራትና ፍጥነት ቀና ትብብት ላደረጉልኝ የብርሃንና ሠላም ማተሚያ ቤት ሠራተኞች ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

## መታሰቢያነቱ

ለሰው ልጆች ሕይወት ከበሬታ ላላቸውና

ሰላምን ለማስፈን ለሚታገሉ ወገኖች ሁሉ!

## ማውጫ

ምስጋና ........ 2
መግቢ፥ ........ 7
ክፍል አንድ ........ 9
ቅመራ! ........ 9
ሰይጣን - ሲዘምር ........ 10
«የጥንቸል - ራስ» ........ 11
እሳት - ከቤት ........ 15
የዳር - አገሩ ........ 16
አንድ ደቂቃ! ........ 19
ሰማየ - ሰማያት ........ 22
«ከሀገሩ - የወጣ» ........ 28
ክፍል ሁለት ........ 31
ፈጠራ ........ 31
ኢትዮጵያ! ........ 32
ይድረስ ........ 33
በየኔነት ........ 36
አንድም - ነገር..... ........ 37
«አምጪ - ወሳጅ» ........ 38
ጥርሴን ምከሩልኝ ........ 45
ብዕረኛው ........ 49

አንድ - ቀን ........ 51

ዓለም - ዕድሜውን ........ 59

የታሪክ - ሕግ ........ 60

ሥርግ ........ 61

መላ - መላ! ........ 63

የአንዳንድ - ሰው ........ 67

«ከመፈቅፈቅ - ማለቅለቅ» ........ 68

«አንተ» ማለት ........ 72

ዕርግማን! ........ 75

የልቤ - ልብ ........ 78

ባይፈትኑኝ ........ 79

እስቲ - ይሁና! ........ 80

ማን ይሰለፍ? ........ 84

ክፍል ሦስት ........ 85

ቅምሻ! ........ 85

ነገርን - ባጭሩ ........ 85

መናቅ ........ 87

ተረብ ........ 87

ለ - ጥጋብ ዘመን ........ 88

ለ - ፍቅር ........ 88

ማሽኮርመም ........ 89

ለ - ማድነቅ.......................................................................89
ለ - ወንድ አደር...................................................................89
ለ - ቅናት ..........................................................................90
በ - ስውር ..........................................................................90
ለ - ምልጃ........................................................................... 91
ለ - ነገረኛ........................................................................... 91
ለ - ራስ ወዳድነት ...............................................................92
ሀገርን - ለማዳን..................................................................92
ለ - ቁጭት ..........................................................................92
ላለ - መጨቆን.....................................................................93
ለ - ጅገና ............................................................................93
ለ - ማስቆጣት ......................................................................94
ስለደራሲው በጥቂቱ ..............................................................95

# መግቢ፥

ለኪነ - ጥበብ የሰገደ ልብ በምዕናባዊ ስርስራ ጥልቀት በውስጡ ጠፍቶ ይሰነብታል።

የሚፈልገውን ሆኖ የሆነውን ይዞ ለ «አደባባይ» ለመብቃት በሚያጋጥሙት ስርፀታዊ - ዕውከታ በ «ገመስጦ - ንትቀት» እሱነቱን ይነጠቅና የአንድ ሰሞን «ዕብድ» ይሆናል። «ምን ይሄ.....» እስከሚባል ደርስ።

ከልባዊ ፈቀሬታና ከበሬታ በመነጨ ውስጣዊ ጭንቀት በምፈለቀቅ ኪነ - ጥበብ ዕርካታን የማላበስ የማስጨነቅ፣ የማስጠበብና የማስጀገን ውበቱንና ጉልበቱን የማገናዘብ ጥበቡም በበዚያው ሰሞን «ዕብደቱ» ይካተታል።

«.....ኑሮን ውትብትብት ጠልቀን ሥርስረን ገብተን አገኘን የምንለው ፍሬ ሃሣብ መጥቀን አውጥተን በአደባባይ ስንገልጥ ‹ቃልን› በውበት በድምቀትና በአክብሮት እንዲንፀባረቅ ከአደረግነው - የፍታችንን ፀንሰን አሳልፈናልና ‹ቃልን‹ ገደፍክ አንባልም» ሲሉ ዕውቅና በሚለው ባለ ቅኔ ፀጋዬ ገ/መድህን «እሳት ወይ አበባ» በሚለው መድብለ ግጥማቸው ላይ ያሰፈሩት የውስጠ - ሕይወት፥ ግንዛቢኤ ምጥቀት የአያሌ ክንውኖችን ውስብስባነት ባህርይ የሚገልጽ «ለአጓ» ነው።

እኔም ይህንን «ፍሬ - ሃሳብ አመኔታዬ በማድረግ ውስጤን የተፈታተንኩበትን ሙከራ ከ«አደባባይ» አልነፈግሁም።

«የያዝነውን - ከወረወረ.....» እንደተሰኘው ከ«እኔ - ይውጣልኝ» በሚልም ስሚዔት ሳይሆን ለጥበቡ ሲሰጠው ከሚገባ ከበሬታና ፍቅር ጭምር «አንድ - ቀን»ን ከ«የኔ ጋሽ» ለጥቆ ይዤ አቀርባለሁ።

የ«አንድ - ቀን»መድበል ከራስ ኪነ - ጥበባዊ ጽንሰ ፍልቀት ባሻገር አንድ እንግዳ ነገር ባይቆጠርም በስፋት ያልተለመደን ባህሪ በመጠኑ እንድታካትት ተደርጋለች።

«ይመጥናሉ» ያልኳቸውን አንዳንድ ተምሣሌታዊና ዘይቤያዊ አነጋገሮችን በመውሰድ በኪነ - ጥበብ ቋንቋ ተቀምረውና ተውበው ሲዘጋጁ እጅግ ጥቂቶችን ያለምንም «ቅንጭብታ» እንደ የ-ምታቸው ስሜት ለ«ቅምሻ» በማቅረብ የትውስታን ባህል ለማዳበር የበኩሌን «አንድ» ብያለሁ።

መለመድ ያለበት «ቁም - ነገር» ስለመሰለኝ።

ስለዚህም «አንድ - ቀን» በቅመራ - በፈጠራና - በቅምሻ- አቅርቦት ለምንባብ በቅታለች።

«ቅመራ» በተለምዶ ወይም በዕለት ተዕለት ቋንቋ ሲነገሩ የቆዩትን ሕዝባዊ አባባሎች ወደ «ግጥም» ለመለወጥ የተጠቀምኩበትን ኪነ - ቋንቋ የገለጽኩበት ስያሜ ነው»

ክፍሌ አቦቸር (ሻምበል)

# ክፍል አንድ

## ቅመራ!

እንዳለፈ - ሣያልፍ
በ «ሰለቸ» - ሣያርፍ
እንደ - ነበረ
ለማኖር
ከወራሻ - ወራሽ
ለማዞር
እንደ - መጣ
ለማጣመን
እንደ - ዘመነ
ለማዘመን
መጨነቅ ነው
መጨነቅ !
መጨመቅ!
በ - ቅመራ!
ኪነ - ሕይወትን ሰርሰራ!

# ሰይጣን - ሲዘምር

ሲ - በለው

ሲሲ - በለው

በለው! በልው!

«ይላል» አሉ ሰይጣን ሲዘምር

ከሲ - ሲ - ሲ፣ - «ጀባው» ሲዘይር

አንተም እየዘመርክ ነው?

እኔን «ሰይጣን - ነው» ያለህ ማነው?

እንደ - ሰይጣን - ከመዘወር

ሰይጣን ሆኖ - መዘመር!

# «የጥንቸል - ራስ»

መቼስ፡-

ነፍስ አይደል? ነፍስ

«ለባለ - ነፍስ....

እና

«ነፍስ» ብጤዋን አንጠልጥላ

ምናምን - ምን ነገሯን ጥላ

ከዘር፥ ዘር - ውርሷ

ከዕትብት ጥሎሽ ልብሷ

ከ «ከገመናዋ» - ጭካ

እንደ - አንዳች ተፈትልካ!

ልቧን እንደ ጆቢራ

እንደ - ሣንጃ ወድራ!

ጆሮቿን እንደ -ጅብራ

እንደ ጃንጥላ - ወጥራ!

ብርር - ር.....ብርር - ር..... እያለች ብርር - ር -!

ቀም! እመር! እመር! ቀም! እመር!

ደሞ ብርር - ር....- ር

ቀም! ዞር - ዞር - አየት

«ማን - አየኝ?» ዓይነት

እንደ ገና ብርር - ር...ቀም! እመር ቀም! ዞር - ዞር

እመር! እመር!
እያለች፥ አንዲት «ብጥሌ» ነገር
የነጠረች - እየነጠረች - እንደ - ኳስ
ብርር - ር.....ብርር - ር እ - ልም! እያለች
እንደ - ነፋስ!
ጉድባ - ጉድባውን.....
ሜዳ - ሜዳውን ጥሻ - ጥሻውን - ጥሳ
ምና - ምኑንም በጥሳ
ትሮጥ!.....ስትሮጥ!....
የ«ነፍስ» አድኗን ስትሮጥ
ድፍን አገር ባላባት...ከደኑ ንጉሥ ፍጥጥ!
ፍጥጥ! ነዋ! ፍጥጥ!
ፍጥጥ! አንዲት «ምንትስዬ» ነገር
ከ«አያድርስ»! ዓይነት....ግዙፍ! ፍጡር
አይ - አበሳ!
አበሳ! ነው አበሳ!
ጥንቸልና - አንበሳ!!
እናም - ልበ ደንዳኔ
ማን? በ«እንደ - ኔ» ዓይነት ወኔ
ራመድ! ራመድ!
ጐራደድ! ጐርደድ!
ገልበጥ!.....ገልበጥ!.....

«ምንትስዋን» - ገልመጥ!

አደረገና....አጅሬ!

ምንድነው - አንቺ ዛሬ?

የሚያስከንፍሽ - ፍንቅሎ

ቆሌሽን እንዲህ አስጥሎ?

******

ወይኔ - ጉዴ!

ጌታዬ! አንተ ቆመሃል እንዴ?

የጫካው የደኑ ንጉሥ

ከዚያ እስከዚህ ድረስ

በ«አንበሳና - ዝሆን» ጨክኖ

እንዲገደሉ - ወስኖ

ይኸውልህ ጌታዬ!

ያገር ጫካ ያገር ደን

እንደ «ጉድ» ነው የሚታደን

********

እሳ!

ታዲያ አንቺ «ዝሆን» ነሽ? ወይስ «አንበሳ?»

ወይስ ለሞትሽ

«መተለቅ» ን ፈልግሽ?

*******

ምን - ይታወቃል! ጌታዬ!

ምን - ይታወቃል!

መ - ጠ - ር - ጠ - ሩ ይበጃል!!

ደሞም ጌታዬ - ቢሆንም

ከ«ዝሆን ጭራ - የጥንቸል ራስ»

ሲሉ አልሰማህም?

# እሳት - ከቤት

ከ«አንተነት»ህ፤ ውስጠ - ሕይወት.....
ከእምነት ልብህ ሣትላቀቅ
«እሱነቱ» - ልብ ጥለቅ!
ም - ጠ - ቅ!
ከጠላትህ «አንድ» ጊዜ -
ከወዳጅህ «ሺ» ጊዜ - ተጠንቀቅ!
«ይላሉ» አበው አሉ
«ያጐረሱት - ሲነክስ
ያቆረቡት - ሲረክስ» ዓይነትን ሲስሉ
«እሳት - ከቤት፤ ጠላት - ከጐረቤት»ን ሲመስሉ።

*******

# የዳር - አገሩ

ሰውዬው አሉ

        ሰውዬው ገራ - ገሩ

የዳር - አገሩ

ንብረቶቹን

ከ«ጋጣ» ነድቶ አህዮቹን

ከመስክ ወስዶ ሲያሰርማራ

«አፊ - ላማ» ስለፈራ

ከሰው ግጦሽ ከሰው ማሳ

        ወሰን አልፈው እንዳይበሉ

ከይዞታው ውጪ ሆነው

        የነገር ጦር እንዳይስሉ

እንደ ወጉ - እንደ ባህሉ፤

        «ሕግ» ሆነና - ለሁሉ

እንደ ወትሮ የብልጠቱን

ካመለኞች አንድ ሁለቱን

በገመድ ብጤ ሸንክሎ

ለቀቃቸውና ለግጦሽ - እሱም ወደ እሱ ውሎ

ወደ ቁፋሮው - ተደፋፋ!

አፈር ሊስብ፥ አፈር ሊገፋ!
ሲማስን ውሎ ውሎ ሲመለስ
ከአኖራቸው መስክ ሲደርስ
ለካስ አንደኛው - ያመሉን
በጥሶ ኖሮ - ገመዱን
የሰው ነዶ - ክምር ሲጥል
ከአውድማው ላይ ሲዘነጥል
ሰውዬው
　　ገራ - ገሩ
የዳር - አገሩ
አዝኖ ተክዞ አየው
«አፊ - ላማ» ስላቆየው
　　ታዲያ - ሰውዬ!
　　ሆዬ!.....
　　　　ቆመጡን መዥረጠና ከነገመዱ የቆየውን
　　　　«ነረተው» አሉ «መናጆ»ውን
　　　　እንዲያ ሆኖ አምሮ
　　　　ሰዎች ለካስ - ያዩት ኖሮ
　　«እንዴ - ዬ!
　　ሰውዬ!

ምነው? ምነው? እባክህ - ምነው?

የበጠሰው ቀበጥ ሳይደርሰው

ከነ ‹ገመዱ› የቆየህን

እንዲህ አድርገህ የዥለጥከውን?»

ቢሉት....

«አ - ዬ!

እናንተ - ዬ

ባታውቁት እንጂ እንደኔ - ሽማቂው ይሄ ነበረ

«አልበጠስ» ቢለው ነው አጅሬ! እንዳለ ሆኖ የኖረ

«በል! - በል» ያለው ይሄ

«ሲያናፋለት» ውሎ የቀረ

ያ - ማ ለይቶለታል፣ ከርሱ ጋር ምን አባረረ?

«አለ» - ይባላል እናንተ - ዬ!

የዳር - አገሩ ሰውዬ

ገራ - ገሩ

የዳር - አገሩ

******

# አንድ ደቂቃ!

በ - «ግዚሀር»

አንተ - እግዚሀር

አንድ ነገር ልጠይቅህ

እና - ንገረኝ

ሣትደብቀኝ

*******

እሰየው! ነዋ! እሰየው!

እንዳልከው ይሁን - ሰውየው!

ጠይቀኝ

ምን ጨነቀኝ!

*******

ከድርሻዬ

የ«ወር» ዓመት ደርሷል ዕድሜዬ

ከማንም ምንም ሳልሻ

ወደዚያ ወደዚህ ሣልዞር

የኖርኩትን ያህል ኖሬ

ያልኖርኩትን ግማሽ ለመኖር

ንገረኝ

ስንት ዓመት ነው የምቀረኝ?

******

ያልከውን እንዳልከው ትቼ

ያንተኑ ላንተ አሰልቼ

«አንድ ደቂቃ» የ - ኔን አንስቼ

ከ«ወርህ»

ግማሽ ዓመት ነው የሚቀርህ

******

ያንተ ደቂቃ ሲቋጠር

ስንት ነው በ - ኔ ሲወጠር?

*******

ሳይነ - ካካ

በ«ሠላሳ» ዓመት ነው የሚለካ

********

የ- ኔስ ‹ሰላሳ - ሺ» ብር

ባንተ - ሰሌት ባንተ - ቁጥር?

*******

በ - ኔ

«አምስት - ሣንቲም» ነው ለ - ኔ

*******

በ - «እግዜሃር»

አንተ - እግዜሃር!

አንድ - ነገር ልጠይቅህ!

ፈቃድህ ሆኖ ተለመነኝ

እባክህን!
«አምስት - ሳንቲም»ህን «ጀባ!» በለኝ?

********

እሺ - ውሰድ
ከጠበከኝ
«አንድ - ደቂቃ» ከታገስከኝ?

# ሰማየ - ሰማያት

አባ - እንደምን አደሩ?

ሠላም - አነጋ መንደሩ?

ደህና!......ደህና!

ደህና - ነን.....ልጄ!.....ደህና!

እግዜር - ካለ

ምና - ለ?

ይመስገን ነው፤

ይመስገን ነው ልጄ!

አንተስ - ወዳጄ?

*******

ተመስገን ነው አባቴ!.....

እኔም ይኸው አለሁ

እንዳለሁ!

********

ምነዋ በል.......

በሰማይ ከምድሩ ሳይላቀቅ

ምሽቱ ለቀን ተራ ሳይለቅ

ወዴት ኑሩዋል በል የምትዋብ?

በሃሣብ መጫኛ የምትሳብ?

********

እኔማ - ይኸውሎ!

የሕይወት «ወግ» እንጉቻ

ናፍቆኝ «ሥስት» ጉልቻ

ቆጥ - ቁርበቱ.....ቢፈትነኝ

አገኝ ብዬ - የምትሆነኝ

ከእንጨት - ሰባሪ ሰብሬ

ከእረኛይቱም - አብሬ

ውሃ - ስትቀዳ - ተሸክሜ

ልብስ - ስታጥብ - ቀድሜ

ያገር ገበያ ስቆጥር

ጥምቀተ ባርህ - ስከትር

እንቁጣጣሽ - በመጣ

ሥራዬ ሆኖ ደፈጣ

ከሠርገኛው - ሠርገኛ - ሆኜ

ካዘንተኛውም - አዝኜ

በፎሌ «ገዳ» በረሣ

በአድባር በ«ጨሌ» ፈጫሣ

አንዱን ስጨርስ ሲታከል

ጋሜ ሳዱላ ስከተል

በፉጨት ዜማ - ብጠራ

የቅኔ ቅኝት - ባበራ

አለሁ የምትል የማያት

አንድም አጥቼ ለ - ኔ ምላት
እና!
ይኸውሎ አባቴ!
ቆላ፣ ከደጋ - ሲያሳድደኝ
«አንባ» አስሼ ቢታክተኝ
ችግሬ ከርስዎ ጣለኝ።
አባቴ.....
አሁንስ በቃ! - ደከምኩኝ
ከጫማዎ ሥር ወደኩኝ
ከንግዲህ እርስዎ ያማጡኝ።
ተባረክ! - ልጄ ተባረክ!
የእግዜርን መንገድ ከአወክ!
ፈቃዱ ሆኖ የጌታ
ችግርክን በኔ - ለረታ!
ምሥጋና - ይግባው በስፋት
በሰማየ - ሰማየ - ሰማያት
ለሰማየ - ሰማየ - ሰማያት
እንትፍ......እንትፍ እንትፍ!
አሜን!
ልጄ - ሆይ!.....
ፈቃዴ ሆኖ ፈቃድህ
«ይቺ - ነች» ያንተ እንድልህ

የቷን - ፈቀደ - ልብህ?

******

ውበቷ - በውበቴ

የእናቷ ሙያ - በማጀቴ

የዘር ዓመሏ - በጉልበቴ

ሁሉም - ለእኔ

ሁሉም - በእኔ

ይካሣል!

ይ - ካ - ሣ - ል!!

ብቻ -

ስበላ - የምታገሳ

ስሰባ - የምትከሳ

ስወድቅ - የምትሰበር

ስመታም - የምትቀበር

እሷን - ነው!

እሷን - ነው! አባ - ይኸውልዎ!

እባክዎ! እንግዲኢህ እባክዎ!

********

አዬ - ልጄ!

እንዲህ ዓይነቷማ - ቅድስት

ምድራዊ ሕይወት ሕብስት

ካ - ለ - ች

እውነትማ - ከተገኘች
«ይቅር» ይበልህ ልጄ!
«ይቅር» ይበልህ ዳግም እንዳታስባት
ብታይህም - እንዳታያት
በስመ - ሰማየ - ሰማያት
ለሰማየ - ሰማየ - ሰማያት
እንትፍ! እንትፍ!
አሜን!
ተው! ልጄ ተው!
ይቺ «ቅድስት»፤ «ቅዱስ» ነውና የታሰባት
እግዜሩም አይፈቅድ ላንተ
በልብህ እንዳታስባት
ና! - እጅህን ስጠኝ ልጄ!
ይቺን ልጅ እንዳትረሳት
በቃ! ገዝቼሃለሁ
ለሁሉም እንዳታነሳት!

*******

ለምን - አባቴ? - ለምን?
ለምንድነው - የማላስባት?

*******

እኔ - ስለማገባት!!

*******

በስመ - አብ!

እህክ! እንትፍ!

ምነው - አንቱ?

የሚሳሳቱ!

እውነት ይሄ ቃል

ከ«ባህታዊ - ነኝ» ባይ አፍ ይወጣል?

*******

ይወጣል!

ይወጣል ልጄ! ይወጣል!

ይወጣል አልኩህ ይወጣል!

ከሞተ «ፃድቅ» የቆመ «ሀጥዕ» ይበልጣል!

እንዴ! ምን ነካህ ልጄ! ምነው?

ለካ! «ልጅነት - ጅልነት» ነው?

ኸረክ! ሞኝ ነህና

ለሞትህ የሚሞት ካለ

ለኩነኔህ ጽድቅና

ምን ያደርጋል «ብህትውና!»

ይልቅ - «ይቅር» ይበልህ ልጄ!

«ይቅር» ይበልህ፤

ይቺን ልጅ እንዳታባት

ብታይህም እንዳታያት

በስመ - ሰማየ - ሰማያት

ለሰማየ - ሰማየ - ሰማያት

እ - ን - ት - ፍ! እ - ን - ት - ፍ!

አሜን።

# «ከሀገሩ - የወጣ»

ይገርማል!

«አነር - ነብር - ነበር» ይባላል

ሰምተሃል?

******

ምና - ለ

የማይባል - ነገር የለ

ደሞ - «አነር - ነብር - ነበር» ተባለ?

******

ተባለ!

ማን - አለ?

አቦ! - ምን ነካህ?

ማን እንዳለ ማንም አያውቅ

«እ - ህ» በለኝ «በ - ጄ» በለኝ

ስማኝ ይልቅ!

*******

መልካም!

«በለኝ» ያልኸኝን ልበልህ

ግን እኮ! - እንዴት ልመንህ?

******

ነገሩማ

የ «ኑብር» - ዘር

አንድ - ሣይቀር

ለዕለት እንጀራ - ለዕለት ጉርስ

አደን ወጣና - ሲመለስ፣

አንደኛው - ከመሀከል

አቃተውና «ወንዝ» መዝለል

በዕለት «ዕድል» በዕለት «ዕጣ»

«ቀረ» ይባላል እንደወጣ

*******

«ባ - ጄ!

ወዳጄ

********

ታዲያ ይኸውልህ

ከአያት ቅድመ አያቶቹ

ከእህት - ከወንድሞቹ

ከዘር ማንዘሩ - ዝርያ

ከአባት ከናቱ ጉያ

ከቀየው ከቆሌው - ጠባይ

ከወጉ ከባህሉ

ከነባራዊ ልምዱ አዋይ

በመራቁ

«ነብር - አነር ሆነ» አሉ - ያውቁ

*******

ከወንዝ ባሻገር ከሠፈሩ

እንደ - ወንዙ እንደ - ሀገሩ

በእሱ ቋንቋ - በሱ ሲችል

«ነብር› ሆኖ መኖር ሲችል

በማላምነው በሚያምነኝ ቃል

እንዴት - «ነብር - አነር» ይባል?

*******

ዋ! ያለማወቅ፡-

«ከሀገሩ የወጣ - ከሀገሩ እስኪመለስ

ቢጭኑት አህያ - ቢለጉሙት ፈረስ»

ሲባል

አልሰማህ ኖሯል!?

# ክፍል ሁለት

## ፈጠራ

በ - ውጣ!

አልወጣ!

በ - ተፈጠር!

አልፈጠር

ሕሊና -

በጣር ሲወጠር!

ከምጥ!

ከያዙኝ!.....ግረዙኝ!

ባይብስ?

ፈጠራ! –

መጠበብ! ጭንቁ አያድርስ

በሣቅ! - በለቅሶ!

በሀዘን! - በቁጣ!

ባይከስ!

# ኢትዮጵያ!

ኢትዮጵያ!

የአፍሪካ ቀንድ ምሰሶ

የሰብዕና - ሰብ፤ አስኳል ፅንስ

የተፈጥሮ ፀጋ ባለቤት

የትውልድ ትግል ጥንስስ

የነፃነት ድንግል ደሴት

የጀግንነት ባሕል ቅርስ!

የሥልጣኔ - አውራ!

የቀደምት ታሪክ አሻራ!!

# ይድረስ

ላከበረ -

ላከበሩት

ላፈቀረ -

ላፈቀሩት -

ለጀገነ -

ላጀገኑት

«አንቱ» ነቱን ማረጋገጫ

ያድናቆትን ስሜት መግለጫ

ቃል ቢፈልግ ቋንቋ ልሳን

መዘከሪያ - ዝክረ ድርሳን

ቃል - ቢኖርም ቃል - አይኖርም

ምኞትን - ስር አያስርም

ልብን ስሜት አይቀርጽም

ፍቅርን ስርፀት አይገልጽም

ተብሎ -

አይገደፍምና - ቃል

ጨምቆ ራሱን ያበቃል

ውስቱኡን - ያደማል

ላዩን - ያደብናል!

እንጂ -

ስሩን ያድናል!

እናም.....

«ነዶ ተቃጥሎ ለበራ

የትውልድ ፍሬ ለዘራ

ለስርወ - ፍሬው አዝመራ

ለባለ - አደራው አደራ!

«ሠላምታዬ -

ላንተ ይድረስ!

ታላቅነትህ -

ይወደስ!»

ብዬ የልቤ

ይንገስ!

ወድቆ - ላቆመኝ - ጋሻዬ

ሞቶ - ላኖረኝ - ጀግናዬ

ለክብር - ለመድረክ - ማማዬ

ለሕይወት - «አቻ› - ሻማዬ

ይድረስ ለክቡር

ክቡር!

ለአለኝታዬ -

ይድረስ! –

ለስርወ - ፍሬው አዝመራ!

ለባለ - አደራው አደራ!!

የሄድክበት - መንገድ - ይጥራ!

የዋልክበት - መድረክ - ይድራ!

ያደርክበት - ምሽት - ይብራ!

ድል - ይደገስ!

ሠላም - ይንገስ!

በአንተ - ጐራ!

በአንተ - ሥራ!

ብዬ ምኞቴን

ላብራ!!

ተስፋዬን - ልዝራ!

የፍጻሜው - መልስ

«ጐሮ ወሸባህ!» - ይድረስ!!

ይድረስ!!

*******

# በየኔነት

ከመልክአ - ምድር
ፍቅር
ከፍቅር አንድነት -
ይወለዳል
ከአንድነት ሠላም -
ይታደጋል
ከሠላም ውበት -
ይበጠራል
ከውበት ጥበበ -
ይፈጠራል
ጥቃት በትግል -
ችግር በጥረት ይነቀላል
ሞት በልደት -
ይበቀላል
ሁሉም በ«የኔነት»
ሁሉም በወንዝ - ባገር
በዜግነት - ወዝ!
አፈር!

# አንድም - ነገር.....

«ሰኞ» ሲመጣ - «ሰኞ»
«ማክሰኞ» ም ያው እንደ - ማክሰኞ
ሰኞ፣ ማክሰኞ ረቡዕ.....ሲያሰኝ
በዘልማድ ቋንቋ ሲያስጠራ
እሱ ግን.....
አንዴም አንድ «ሰኞ»ን አንድ «ማክሰኞ»ን
በውስጡ አላባራ!!
ስንት ቀን በቀን
ስንት ዘመን - በዘመን ሲያልቅ
አንድም - ቀን አንድም - ዘመን
ራሱን መልሶ አያውቅ።
«ትላንት»ና - «ዛሬ»ን ሣይሆን
«ዛሬ»ም - «ነገ»ን ሳይመስል
«አምና»ም - «ዘንድሮን»ን ሣይሆን
«ዘንድሮ»ም - «ከርሞ»ን ሣይወክል
«ሰኔ»፣ - ያው ያመቱ «ሰኔ»
የ«ዘንድሮ» - «ሰኔ› ሆኖ ሲያልቅ
አንድም - «መስከረም» - ያምና «መስከረም»
የ«ከርሞ» «መስከረም» ሆኖ አያውቅ።
ስንት ነገር - በነገር
በ«ይለፍ - ይለፍ» ሲተላለፍ
ስንት ጊዜ - በጊዜ
ዘመን - በዘመን ሲሸራረፍ
ሁሉም - በስም.....
በስም እንጂ ሁሉም በስም
አንድም - ነገር አንድ ዘመን
ራሱን መልሶ አያውቅም።

******

# «አምጪ - ወሳጅ»

ሀገርኛ
ባህርኛ
ምንም ይሁን
ከየትም ይምጣ
ይሁን እንጂ - የሚጠጣ
ከምሽት እስከ ንጋት
«መጠጣት ነው» አሉ መጋት
እናስ!
ወዳጄ - ታዲያስ?
በወዳጆችህ - ትባላለህ
አንተስ - በአንተ
ምን ትላለህ?
*******

ላልተደበቀ - ሣልደበቅ
ላልተሰረቅ - ሣልሠረቅ
ሀገር አውቆት
ሀገር መርቆት
በአደባባይ - ከወጣ
በአደባባይ - ብጠጣ
የመስከሬ ወሬ ሆኖ፥
የ«መጠጣቴ» ነውሩ
ምኑ ዘንድ ነው ወዳጄ!
የ«ትባላለህ» ሚስጢሩ?
******

እኔማ - ምን አውቄ
በወዳጆችህ ተደንቄ
እድነሚያሙህ - እንዳላማህ
ወዳጅነቴን ነው - የማበራህ!

*******

ለስርቻው «ሰንደቅ» መስለው
ለ«መስከ» ውሎ «ድብቅ» ሆነው
በዝጉብኝ
ሸፍኑብኝ - ተሸፋፍጠው
በውስጣቸው - ተሸጉጠው
«ጋን» አጣሪ - «በርሜል» ገልባጭ!
«ዱር» አዳሪ «ጠርሙስ» ጨላጭ
እነዚህ ናቸው፥ የኔ ወዳጆች!
«ጠጪ - ነው» የሚሉኝ ሰካራሞች

*******

በሙቶ - ሙቶ የምሰ'ላ
ያን - ሁሉ ደመወዝ እየበላ
«ወር»ም አይደርስ ገንዘብ የለው
የሚኖረው በ«ሞዴል» ነው
«ይሉሃል» አሉ - ያዝካቸው
ኪስህን - ያዳሰስካቸው
እናስ!
ወዳጄ - ታዲያስ?
ይሉሃል
የምትለው - ይኖርሃል?

*******

እንካ - ለእንካ - ቅብብሎሽ
የሕይወት አኑር ሽቀላ
በልክ - አያውቅ የጭካኔ ዝርፊያ ጥላ
እንደኔ ዓይነቱ ሲያጠላ
«መላ» ብዬ መለ - መላ
ጐደጐደ - ወጭቴን
ገበታዬን - ልሞላ
ማንንም ሣላሣንስ
እኔ - የእኔን ባቀናንስ

እስቲ - ምን ከፋት
ምን ወንጀል አለው?
ሞዴለኛ - ነው» የተባለው?
*******

እኔማ ምን አውቄ
በወዳጆችህ - ተደንቄ
ያሉህን - እንዳልልህ
ቁጭቴን ነው - የምነግርህ!
*******

እንግዲያማ ወዳጄ ሆይ!
ደመወዜ - ነው ደመወዛቸው
የሰጠኝ - ነው የሰጣቸው
መወያዬ - መወያቸው
ከተማዬም - ከተማቸው
ሆኖ ሣለ - የኩሌታ
ነጋሪቱ - የተመታ
መኖር - ለእኔ ካመረረ
ሊነሱ - ምን መነዘረ?
ፈቀሬታን ፍቅር ነስተው
አመኔታን - ዕምነት ነፍገው
አስልቶ ካዝና - ሰርስራ
በ«እጅ - በሉ»ን እንደ ሥራ
«ሙጢኝ» ያሉ - ሙጢኛሞች
ሰነድ ደላዥ - ዘራፊዎች
እነሱ ናቸው የኰነኑኝ
«ሞዴለኛ - ነው» - የሚሉኝ
*******

«ዕብድ - ነው» ይላሉ «ዕብድ»
ዓመሉ ከአመል የማይለምድ
እናስ?
ወዳጄ - ታዲያስ?

ብለው! ብለው! ለተባለ
የምትለው ነገር አለ?
******

ሣልጅቡነው
ራሴን «ባጉል» ሣልጀንነው
ለጆሮ ለዓይን....ለበቃ
«ይፋ» ሆኖ የኔ ቋንቋ
ድንቀኛውን «ድንቅ!» ማለት
ሀገሬውን አባ - ቢያ!
አያህውን አንተ - አህያ!
ሸፋጩንም አንተ ሸፋጭ!
ብዬ - በግላጭ
በቃ!
ጨዋታ- ነው ንፁህ ፍቅር
በቀል - በውስጤ ሳልቋጥር
ታዲያ -
ጠቢበጥኛው - እንዲጠበብ
ልቅ፥ ልቁ - እንዲታቀብ
ማድረጌ ምን እንከን አለው
«ብልስ»ን - ከ «ጥሬ» - ለለየው?
ወዳጄ!
እስቲ - በሞቴ!
እምኔ - ላይ ነው ዕብደቴ?
********

እኔማ - ምን - አውቄ
በወዳጆችህ - ተደንቄ
በወዳጆችህ - ተደንቄ
እንደሚሉህ - እንዳልልህ
እኔነቴን - ገለጽኩልህ
*******

ወዳጄ!

ጥርሳቸው ለዕለት ገልፍጦ
ሆዳቸው ዓመት የሚያቄም
ውስጣቸው በቀል - የሚያዜም
ሴረኞች ናቸው መርዘኞች!
«በሹክሹክታ» - የሚገድሉ
ግልጽነቴን «ዕብድ!» የሚሉ።
*******

«ሃጅ - ነው» ይላሉ «ሃጅ»
ወጥቶ - ወራጅ
ሴሰኛ - ነው ዝሙት ወዳጅ!
እናስ!
ወዳጄ - ታዲያስ?
ለሚሉት ምን ትላለህ?
ትባላለህ!
********

ለወደድኳት - ለወደደችኝ
እንዳመንኳት - ላመነችኝ
ግልጽ ሆኖ - የኔ ፍቅር
ሕሊናዬን - ሳልመሰጥር
ከአንድ ሌላ ሌላ ሳላይ
በየመስኩ - በየአደባባይ
አንዲትዬን -ይዤ ብታይ
እኔ ሣውቀው -
የኔን ያህል
«ወግ» - መሠለኝ -
የዓለም - ባህል
ላንድ - ላንዴ - ከታማሁኝ
«ሴሰኛ - ነው» - ከተባልኩኝ
አንድ - ኮከብ
በአንድ - ጀንበር
ስብስቡ - በሚቆጠር

በየ - ጥሻው በየ - ጥዱ
ዘጠኝ አስር - የሚነዱ
እነዚህ ናቸው - የሚያኝኩኝ
«ሴሰኝነቴ»ን - የሚነግሩኝ
«ቀልድ - ያበዛል
ሥራ - ያዋ'ዛል
አሿፊ ነው ተረበኛ
ተረት - ደራች አዚመኛ»
ይላሉ
አሉ!
እናስ
ወዳጄ - ታዲያስ?
ላሉት ነገር የምትለው
ምንድን - ነው?
*******
ስንት ቁም ነገር ተናግሬ
አንዱንም አልሰሙልኝም
ታላላቅ ሥራ ሠርቼ
ከምንም አልጣፉልኝም
ግና -
ከቁም - ነገር ንግግሮቼ
የ«ትንታ» - ተረቶቼ
ከድንቅ - ድንቅ ሥራዎቼ
ብናኝ ያህል ስህተቶቼ
እነዚህ ናቸው ልበል!
ለሕሊናቸው የሚገዙ?
ለአዕምሮ «ድፍኖች» የሚያዙ?
*******
እኔማ - ምን አውቄ
በወዳጆችህ - ተደንቄ
ነገሩ ሁሉ - ቢገርመኝ

ወዳጅነቴ - አስለፈለፈኝ
*******

ወዳጄ -
ሰማኸው፤ አየኸው አይደል?
የሥሜን - «ስም» ጐዶሎ
የመዋያዬን - ተረፈ ውሎ?
ከእንግዲህ -
«መጪ - ሂያጅ
አምጪ - ወሣጅ» ነውና~
እንደ - መጣህ ድረስላቸው
እንዳመጣህ - መልስላቸው
የኔንም ዕውነት ይዘህላቸው
ከዚያ፡-
አልመጣባችሁም - አትምጡብኝ
ብያለሁና - ተባባሉልኝ።
ቻው!!

# ጥርሴን ምከሩልኝ

ተው! በሉት ተቆጡት -

አይሆንም በሉልኝ

አቦ! ንግሩልኝ

ጥርሴን - ምከሩልኝ

እንደ «ቀን» እንደ «ሌት» -

መኖር ይልመድልኝ

«እህ» ብሎ እንደ «ሰንባች» -

እንደ ኗሪው ሆዴ

«ህ» ብሎ እንዲያድርልኝ -

ንገሩልኝ ዘዴ

ደርሶ ቅብጠት እንጂ -

ዳሩ ምን ሆነና

ምን - ተበደለና?

ከፅሬት የመረረ -

የከበደ ጫና

ምን አውጥቶ አውርዶ -

ምን ተሸከመና

«ሆዴ» የቻለውን -

«ጥርሴ» ምን ቻለና

ትሎ «ብልጭ! - ድርግም!» -

መከፋት አጠና?

ስንት - ምናምንቴ

ተሞልቶ - በአንጀቴ

ስንት አንኩሮ ንፍር

በውስጡ - ሲጨፍር

ነገር - ሲሰልሰው

መች ከበደኝ አለ -

«ሆዴ» መች «ሆድ» ባሰው?

የቅርብ የሩቅ ዘዴ

ሚሥጢር ዘልቆት ሆዴ

ሁሉ ነገር ገብቶት

መተው መቻል ሞልቶት

ደስ እንዳለው - ፈክቶ

እንደ ጠጣ - ረክቶ

እየ - ተበደረ

ተርፎት - እንዳደረ

እንዲያ ሆኖ እንጂ ነው -

«ሆዴ» የለመደው

ለተቆጣው - ቁጣ!

-ለዱለኛ ዱላ!

-የት አባቱ ያውቀው?

ብቻ፡-

አሁን ብቻ - ደርሶ

የጥርሴን - ተውሶ

ድብቅ ጠባይ - ለብሶ

የእልህ “እሳት - ጐርሶ!

አይሆን ነገር ቅጂ

በራስ ፈቃድ ማደር

ዐመል አወጣ እንጂ

የሁላችን -- ትንሽ--

ይህ ጥርሴ ከመጣ

ጥሬ ብስል አውቆ

ለውበት ከነጣ

ሆዴ “ሆድ--ባሻ!

“ሆደ--ቡቡ !” ሆነ ሌላ አመል አወጣ

እናም፡-

ይሄ__ ጥርሴ

አካል__ ገላ ልብሴ

“ዕረፍ”__ ሲሉት ማረፍ

“ቻል” ያሉትን “ችሎ”

መኖር “አልችል” ብሎ

ከዘመድ ከወዳጅ__

አለኝ ከምለው ሰው

ባያቀያይመኝ_ባያጣላኝ ምነው?

አቦ_ንገሩልኝ
ጥርሴን_ምከሩልኝ
ሣቅለት ሣቅለት_
ሣቅለት በሉልኝ
እንደ “ቀን” እንደ “ሌት”_
መኖር ይልመድልኝ
ወይ ድብቅ ምኞቱን_
በድብቅ ይንገረኝ
ይህን “ብልጭ ! _ድርግም !”
አሊያም ይተወኝ

# ብዕረኛው

ኳ! ኳ! - ኳ! ኳ!

ማነው?

እንግዳ

አፍ፡- ጥርግ ጥርግ፥

ልብስ - ልብ'ስ - ልብ'ስ

ቆሻሻ_ወደጓዳ!

እንደ «ምን ዓይነት ዕዳ!»

እንደሚባል ዓይነት መንገድ

«መጣሁ! - መጣሁ!» ምንድነው?

«መጣሁ»ን የምታስግድ?

የተከፈተ በር የምትጠብቅ

ጥሰህ ግባ - 'ንጂ በግድ!

ያልተገለጠው እንዲገለጥ

ያልታየውን እንድታየው

«መጣሁ! መጣሁ!»ን ተለየው።

«እንደ - ሚያውቁት».....አት - በለው

ያወከውን ሁሉ አውቋል

ያወቀውን ነው ያወከው

«እንደ - ሚያዩት».....አት - በለው

ያየኸውን ሁሉ አይቷል

ያየውን ነው አንተ ያየኸው
በ«በማን - ልበል - ወንድም?»
ስትቀርበው
«መሰቡን ከነ - ሽፋኑ
እንዴት ያዩታል?» ስትለው
«እንደ - ምታየው - አየሁት
አለላው እጅግ ድንቅ ነው
«ወለላው - የታለ?» ቢህል
እንዳያስቸግርህ የምትለው።
«የሚሉትን» ብቻ አትበል
«እንዳሉት» ብቻ አይበቃም
«መጣሁ! - መጣሁ!»ም
አያጣም
ሂድ! - ና! - ውረድ! - ውጣ!
ግባና - አውጣ!
ውጣና - አምጣ!
የፈለገው - ይፈልግብህ
የሚኮነውን ሁሉ ሁን
የሚባለውን ሁሉ ተባል!
«ብዕረኛው» አሉ....እንዲባል!!

# አንድ - ቀን

የእኛ - እማማ!

የእኛ - ማማ!

መዋቢያሽ ሽማ!

መድመቂያሽ መታያ - ዓርማ!

በእኛ - ግዳይ! በእኛ - ሙያ

እኛን - ማያ!

እና ታዲያ!

ምነዋ! ምነዋ!

እናት - ዓለም

ምንድን ነው - የሚያሳስብሽ?

ምንድን ነው - የሚያሳስብሽ?

ያልሆነ  ነገር ከቶ አልሆነ

ያልታየ ነገር አልታየብሽ?

ሰቆቃ! እንደ - ሁ፣ የትም - ነበር

የትም - አለ

የአንቺ ብቻ የሚመስልሽ?

ታዲያ -

ምነው - እናቴ ምነው?

የሰማሁትን - ብትሰሚልኝ

ያየሁትን - ብታይልኝ?

ያመንኩትን - ብታምኚልኝ?
የ«ዓለም»ን በር - አንኳኩተሽ
«ዕልፈተ - መኸሩ»ን ብ -‘ዳስሺው
«ገመና»ውን ብታስሺው
ትሰሚው ነበር ትሰሚው
የምልሽን እንድታምኚው።
ለጥፋት «ደም - መና» ጥላ
«ስለት» ለ«ስለት» ያልተ - ሣለ
«ወዳጄ!» ያለው «ወዳጁ!»
የአካሉ የሥጋው ቁራጭ
ጦር ጐራዴ ያልሣለበት
ያልሆነበት ጠላት «አማጭ»
በጥይት - ናዳ! ያልተናዳ
ውጭ ከውስጥ ያልተዳማ
በቸነፈር ያልነፈረ - ያልተራበ ያልተጠማ
አንድም አልኩሽ አንድም
የትም አይገኝ እማማ!!
ለጉስቁል ሕይወት መሬቱ
ለዳቦ ግኘት ያልሣለ
የ«ሠላም» ያለህ? ያላለ
ለአድባር ለቆሌው ያልተሣለ
የትስ? የት - አለ? ብለሽ እናት - ዓለም

በዚች «ምድር» በዚች «ዓለም»

በቀን፡-

በጊዜ ሚዛን ተዳፋት «እሱነቱ» ያልኰበሰ

በደም በሕይወት፥ በዕለት ጥረት

«እንቱነቱ» ያልታደሰ

ከልዕለ ልዕለ - ኃያል ከትላልቅ ትንንሹ

ከዚያም በታች ብትጠሪ

አንድም አይገኝ ብትቆጥሪ።

ምነው! ታዲያ - እናት - ዓለም

እንደ የ«ብቻችሽ» ትከፊያለሽ?

እንደ «ፍፃሜ» ትሰሚያለሽ?

በአጋጣሚ ግጥምጥሞሽ

በቀን ቅኝት በቀን ጥላ

የምኞት ኑባሬ ታሪክ

በአንቺነትሽ ቢያጠላ

መጠቃትሽ «ጥቃት» ቢሆንም

ለአንድ ሰሞን ቢወራ!

«ድል!» ማድረግሽ እንደሆነ

አንድም ዘመን አላባራ!!

«ወዳጄ!» ያልሺው «ወዳጅሽ!»

ወዳጅነቱን ቢያጠፋ

ከ«ከፋ» ጠላት ቢከፋት!

ምን - አስከፋሽ እናት ዓለም
ከመጫሚያሽ ስር ሊደፋ?
የአካልሽ ቁራጭ «አካልሽ»
«ስሙ» የሚጠራ በ«ስምሽ»
በችግርሽ - ላለመቸገር
በመከራሽ - ላለመዘከር
ለእሱነቱ «ከርሰ - ሱታፌ»
በ«ምን - ተዳዬ» ጥሎሽ ቢሸሽ
«ምን - አሉ? «በይኙ» ምን - አለ?»
የአንድ - ቀን «ቀኑ»ን ታያለሽ!
«ቅሪተ - አካሉ» እንደ ቀረ
ክብረ - ሕሊናው ሲሟሽሽ!
አንቺ - ግና
በልጆችሽ የደም «አስኳል»
ጊዜ - ደርሶ ጊዜ - ሲጣል
በፋታ - የለሽ! እልህ - ጥረት
በላብ ጠብታ በሚመረቅ
በውስጠ - ፍክ! ቅን አእምሮ
የመንፈስ ብርታት በሚጠይቅ
ጥቃትሽ በ«ዕልህ« ሲበቀል!
ችግርሽ ሥሩ ሲነቀል!
የደፈረሽ - ተንበርክኮ

ያኰሰሰሽ - ይኰስሳል
ማዕድሽ - በፀጋ ልባስ
መስክሽ በአደይ አበባ!
ጐተራሽ ሞልቶ ይፈሣል!
ዳቦሽ - ይተርፋል!
ይ - ት - ረ - ፈ - ረ - ፋ - ል!!
ፍሬሽ - ይንዥረገጋል
ሠላምሽ - በድል ሲደምቅ
አንድነትሽ «አንድ» ይሆናል!
ሥልጣኔሽ ብልጽግናሽ
በዘመኑ - ይዘምናል!!
ንጋትሽ - እንደ አዳይ!
ምሽትሽ - እንደ - ጨረቃ!
ተራራሽ - እንደ - ሰንደቅ!
ፏፏቴሽ - እንደ ሙዚቃ!
ልብ ይሠርቃል!
ያ - ስ - ረ - ቀ - ር - ቃ - ል!!
ልጆችሽ - ይደስታሉ!
ሕፃናት - ይቦርቃሉ!
አንቺ የሁሉ
ሁሉም - የአንቺ ይሆናሉ!
ያኔ - ታዲያ -

«ብርቅዬ!» - «ድንቅዬ!» ነገር
ትልቃችን ትሆኚ - ና!
ከአድማስ - ወዲህ ከአድማስ - ወዲያ
በድምቀትሽ - ትታይና!
«አቤት!» ባይሽ - «አለው» ባይሽ
ከየምኑ - ይከብሻል!
ያላየ - ሊያይሽ
የሸሸ ይማለድሻል
እመኚኝ አልኩሽ እመኚኝ!
ሙች የምልሽ «እናቴ» ሙች
ሙች አልልሽም ልሙትልሽ!
ጡትሽን ይገቬ ልማልልሽ!
«አንድ - ቀን»
«ዕውን» ይሆናል በምድርሽ!!
እናም -
አልፎ ሁሉም - አልፎ
ዕድሜን የኋሊት ጠልፎ
አላፊ መጪው ተፅፎ!
ያስተዛዝበናል እንጂ
ትዝታው ብቻ ተርፎ።
ያንቺማ ነገር «ዕውቅ» ነው
ፀደይ - ዓለምሽ የሚታመን

«የአንድ - ቀን» ሽ የ«አንድ - ዘመን»
እስከዚያው ግና!
አትከፊ - ይከፋናል
አይጭነቅሽ ይጨንቀናል
ያልፋል! - ሁሉም ያልፋል!
የማያ - ልፍ አንድም የለም
«ቸል» ባትይ «ቻል» አድርገው
የማይቻል አይኖር መቼም
እና....ግድየለም!
ግድየለም አልኩሽ - ግድየለም
<u>የጊዜ ጉዳይ</u> ሆኖ እንጂ
ሰቆቃሽ የ«ዕድል» አይደለም።
ይልቅ!
ለ«አንድ ዘመን» - «አንድ - ቀን» ሽ
እንድሆንሽ
መርቂኝ «እናት - ዓለም» መርቂኢኝ
እንትፍ! እንትፍ! በይብኝ
«አእዋፋት - በዝማሬያቸው
እንስሳት - በእስትንፋሳቸው
ያድምቁህ!
ያሙቁህ!
ዱር - ገደሉ ሀገር - ምድሩ

ወንዛ - ወንዙ ሸንተረሩ

ኃይል - ጉልበት አይንፈጉህ!»

ብለሽ መርቂኝ!

መርቂኝ «እናት - ዓለም» መርቂኝ

እንትፍ! እንትፍ! በይብኝ

የመንፈስ - ጽናት ለምኚልኝ

ተራራውን ወንድም - ጋሻ!

ቋጥኝ አለቱን መስከ አርጊልኝ

የሕዝብ - ፍቅር የሀገር - ዕውነት

«ግራ - ቀኝ» ህ ይቁም በይኝ!

እና - መርቂኝ!

እንትፍ! እንትፍ! በይብኝ።

*******

# ዓለም - ዕድሜውን

አንድ ሁለት..... አስር

ያለ - ምንም ስሌት ቀረሽ

አበቅቴ ቢገለበጥ

የጓሊዩሽ ዘመን ቢፈተሽ

እንደ ወጣ «የወጣ»

እንደ «ቀረ» የቀረ

እንደ ታለመ የሰመረ

እንደ - ሰመረ - የዘመረ

እንዳለ - ኖሮ

እንደኖረ - የኖረ

አንዳችም ነገር የለ

አለ ነበረ

ተብሎ - የተነገረ።

ጠላት - ሆኖ ያረጀ

ወዳጅ - ሆኖ ያፈጀ

እንደ - በጀ እንደ - ጎዳ

እንደ - ጎዳ እንደ - በጀ

ሣይኖር ነው የኖረ

ዓለም ዕድሜውን የፈጀ።

*******

# የታሪክ - ሕግ

«ቦ ጊዜ ለሁሉ»

አለ ዳዊት ማለታቸው

ዛሬ «ትዝም» ባይላቸው

በተፈጥሮ ዑደት ውሉ

«ትዝ» ብሎን ለኛ ቃሉ

-ስንጠብቀው

-ስንሰንቀው

ይኸው «ጊዜ» ው ፈቀደና

የዳዊት «ቦ....» ደረሰና

የ«ታሪኢክ - ሕግ» - ፈረደና

እና ይኸው

እንዲያ እንዳስለፈፈ

ሲመጣ - አመጣጣና

ሲያልፍ - ም ይዞ አለፈ።

******

# ሥርግ

ሰው፡- እንደ አፈር

አፈር - አቧራ!

በአካፋ ዝቆሽ ሲዘራ!

አፈር፡- እንደ - ሰው

ሰው አፈር

ሆኖ - ሲፈርሰው

ቀልጦ - ሲፈሰው

ቋጥኝ፤ አለቱ ሲፋጨው

ምና- ምን፤ ነገሩ ሲናጨው

እያየህ፡-

ትወደኝ እንደሁ አንተ ሰው

ትሰማለህ - የኔ ወንድም?

«በሞትህ!......«ሙት!» አትበለኝ

«ሞት» አልወድም

ዘራፍ! አካኪ ዘራፍ!

«ሞት» እኔን - አይወስድም!

ይላል -

ቃል

ሲኰራ!

ፍርሃቱ ውስጡን -

ስያበራ!

ግንኮ

ዝርግት! - ዝግት! - ክትት!

እስከ ወዲያኛው ባያስቀር

«ሞት!» እንዴት ጥሩ ነበር!!

ማንንም «ምንም»

«አንድ» ሲያደርግ

ለ - ርሱ ግን ሥርግ!

እ - ል - ል!

የ - ሚ - ል!

# መላ - መላ!

እጅሽን ይዞት በእጁ
ሲያነጋግርሽ ከደጁ
ምናለሽ?

ምናለሽ - ልጁ?
መላዬ፥-
መላ - መላ
ንገሪኝ - የኔ - ገላ!

******

እጄን ሰጥቼው ለልጁ
ቢያነጋግረኝ ከደጁ

እንደምንድነሽ - ሰላምታ
ከደህና ሰንብች በስተቀር
ያለኝም - የለ በይደር
መላዬ:-
መላ - መላ
ያለኝም - የለ ሌላ!

******

ከአምባው በአሻገር - ከወንዙ ዳር
ከአረንጓዴው መስክ - ለምለሙ ሣር
ይዞሽ ይዘሺው - ከዛፍ ጥላ

ስቆ ሲያስቅሽ - በከለላ

ልብሽ የልቡን - ባይጠርጥር

ገላ ከገላ - ከተናካ

መች ያጣል ብለሽ - ትንሽ ሣንካ?

መላዬ:-

መላ - መላ

ንገሪኝ - የኔ - ገላ

******

በቀን ገጠመኝ - በቀን ገዴ

መንገድ ሆኖ - ከመንገዴ

አላስችል ቢለኝ - የፍጥረቱ

ቢስቅ ሣቅሁ እንጂ - ለውበቱ

ቢይዘኝ - ይገዬው - በመዳፌ

ቢያየኝ አይቼው - ከማለፌ

ያለኝም የለ - ልጁ ሌላ

አንተው ነህ ለኔ - የኔ - ገላ!

መላዬ:-

መላ - መላ

ያለኝም የለ - ሌላ

********

መች ከፋ ብለሽ - ያፍ ሰላምታ

ጥርስሽ ለጥርሱ - ባይረታ

ልብሽ ለውበት - ከሸፈተ
ጓዙን ጠቅሎ - ከከተተ
ዐይኑን ዓይንሽ ላይ - ካሳረፈው
ለገላሸሽ ጠረን - ካወረሰው
ምን ቀረ ብለሽ - የኔ - ገላ
መላ ነው እንጂ - መላ - መላ

መላዬ:-

መላ - መላ

ንገሪኝ - የኔ - ገላ!

*******

ለሸጋው ፀባይ - ላንደበቱ
ለባህሉ እንጂ - ላከብሮቱ
አይቼው ምነው - አይቼው
ሁሉኡን ረስቼ - ሁሉን ትቼው
አካል ገላዬ - ገላህ ሆኖ
ሁለንተናዬ - ላንተ ሰክኖ
ቆሜ እያየኸኝ - ያለ መላ
ምን አስባለሁ -ካንተ ሌላ
መላዬ፡ - መላ - መላ
ያለኝ፡ - የለ - ሌላ

*******

እጅሽን ይዞት - በእጁ

ሲያነጋግርሽ - ከደጁ
ምናለሽ?
ምናለሽ - ልጁ?
መላዬ፡ - መላ - መላ
ንገሪኝ - የኔ - ገላ!

********

እጄን ሰጥቼው ለልጁ
ቢያነጋግረኝ ከደጁ
ከእንደምድነሽ ሰላምታ
ከደህና ሰንብች በስተቀር
ያለኝም የለ በይደር
መላዬ፡-
መላ - መላ
ያለኝም የለ - ሌላ!

# የአንዳንድ - ሰው

ከነጮቹ

ከጥቁሮቹ

ከሰው ልጆች የአንዳንዶቹ

«ዕጣ» ሆኖ የ«ዕድል» ክፉይ

ከዕልፍ አዕላፍ የአንዱ ሲታይ

እንደ «ቡሬ» ሞፈር ቢስብ

አፈር - ምሶ፤ አፈር ቢክብ

እሳት - ሆኖ፤ እሳት - ቢያምጥ

ጋራ - ንዶ፤ ቋጥኝ - ቢያቀልጥ

ለግንባሩ «ግንባር» የለው

ቅን ምግባሩ «ጐሽ!» አያየው፡፡

ጥሞም - አይጥም የእርሱ አንደበት

«ዕውን» አይሆን የእርሱ ዕውነት

የአንዳንድ ሰው የ«ጐህ» መዳፍ

ቋትሞ የለው ቀሪ ምዕራፍ፡፡

አዬ!

የአንዳንድ ሰው ጥምር ትግል

የባካኝ ሰውነት «ሽፍን» ገድል!፡፡

******

# «ከመፈቅፈቅ - ማለቅለቅ»

«ጣና» ቢታቀብ ከስሩ
ጀማ አንገር በሽሎ
በለስ.....ከሌለ ገባሩ
የሀገር አፈር ፍልቃቂ የጥቁር ወንዝ ፍንጣቂ
የሩቅ - እሩቅ አካላይ
ከሀገር ዘርፎ ከሀገር ኮብላይ
መች ይኖር ነበር መንገደኛው......
መች ይኖር ነበር ጥቁር - አባይ?
ምንጩ ቢደፈርን ከአናቱ
«ቆቃ» ቢቋጠር እንብርቱ
«ከሰም» ቢከስም ቢቀለበስ «ሚሌ» ፊቱ
መች ይኖር ነበር በረኸኛው.....
መች ይኖር ነበር ጭራሽ
«አዋሽ!» የምንለው አዋሽ!
*******
ማንም ከማንም
ምንም ይሁን ምንም
አንዱ ከሌለ ሌላው
ሌላው ካለሌለው አይኖርም
አዝርዕትም «ፍሬ» እንዲሰጥ

«አበባ»ውም - እንዲፈካ
የዛፍ ተክሉ «ቀጥ!» ብሎ
በ«ምሰሶ» - በ«ማዕዘኑ»
በውበቱ እንዲያረካ
ማለዳ ነው ከቡቃያው
አረማሞው - የሚነቀል
ከጥንቱ - ነው ከችግኙ
ጠማሞቱ የምቃናው
«ኮት ኳች» ከሌለ - «አረም« ነቃይ
«ወሣጅ» ከሌለ «ተቀባይ»
ጥሩም መጥፎም አይታይ
እናም.....
ይኸው ነው የኛም።
«ሀ» ሲባል «ሀ» ቢባል
ጅምሩ ቀድሞ ቢዳሰስ
ቀድሞ! ቀድሞ ቢቀነጠስ
መፈልፈያው ቢደፈን
ሥሩ ማለዳ ቢበጠስ
የውስጥ ውስጡ የላይ የላዩ
ቃርሚያው በወጉ ቢነሣ
ባልኖረ ባልነበረ - ነበረ
የዛሬው «ክምር» አበሣ!

ይኸው ዛሬኢም እንዲሁ
ለቆየን ችግር «እርሾ» ሆኖ
እንደ «ጲላጦስ» አንጡኝ የሚል
ውስጡን - በውስጡ - ይዞ
ሲታዘን ቀድሞ የሚዊስል
የችግሩ «ችግር» ይህ ነው
ሽምቅታው ነው የበደለን
የ«ሣመን» ነው የ«ነከሰን»
የ‹ሣቀ› ነው የገደለን።
እንዲያ - ባይሆን
ከወዳጅም ጥሩ ወዳጅ ከጠላትም የከፋ ጠላት
ባይኖርብን....የብብት እሳት
«ቀላቢ» ባይኖር....አሞካች
መሥሪ ባይኖር «መንታ» ምላስ
የሀገር ጉበዝ ጥሪት መቼ ይላስ?
እና - ጉበዝ.....
ያለፈው ቀድሞ አለፈ
ዛሬ ለነገ እንዲነቀስ
ድራ - ድሩን ነው መበጠስ
«አስኳሉን» ነው መፈርከስ
እንጂ.....
ቅንርንጫፉም ጭራሮ ነው

ግንዱ ሲቆረጥ የሚረግፍ
ግንዱም ቢሆን ግንዲላ ነው
ሥሩ ሲነቀል የሚነጥፍ
እና.....
ጉበዝ - በቅድሚያ
የብብትን ነው.....የጉያ
ከመጤ ታሪክ ቅርሻት ከሽፍጠኞች ዕድፍ ለመንፃት
ሥሩን ነው «ሥር» ማሳጣት
በወረስነው አንጃ ግራንጃ
«እንኩ» ባሉን ብንከርምም
እኛም ለ«ነገ» ነው እንዳንደግም
የላዩ የላዩ የአንገት ወዳጅ
«ሽፍን» አሽከላው ሲገለጥ
«አሾክሿኪው» አፉ ሲዘጋ
«ውሻቂው» እጁ ሲቆረጥ
እርቃኑን ይቀራል የጥሻው
የጀግናን ክንድ ሲቀምስ
አፈር ሲለብስ ማንጠሻው
የሚሆነው ዛሬ - ይሁን
አይኑር «ይደር» የምንለው
«ከመንፈቅፈቅ - ማለቅለቅ»
እንዲሉ ነውና አበው!

# «አንተ» ማለት

አንተም እንደ -› ኔ

ለ - › ኔ

እኔም እንዳንተ

ላንተ

እንደ -› ንተ - አንተን፥ አንተን እንደ - › ኔ

ሣይ -› ኔ

　　　　አንተም - እንዲሁ

　　　　ሣይህ ስታየኝ እንደ - ብርቅ

　　　　ግና.....

　　　　ስቀህ፡- ላትስቅ - ስትስቅ

ላትርቀኝ - ርቀህ - ስታምነኝ

ሣትወደኝ - ወደህ - ስትወደኝ

«ወዳጄ - ልቤ» ስትለኝ

እንደ ወደድከኝ ወድጄህ

እንዳመንከኝ - አምኜህ

　　　　መልሰህ - ደሞ፤ ስትመልሰኝ

　　　　ለ«ቅኝት»ህ - ስትስለኝ

　　　　ለ«ስለት»ህ - ስትሣለኝ

ድንገት ባንኜ - ብታገኘኝ

«ሞኝ! ሞኝ! - ነህ! ሞኝ!»

ብዬ ብልህ ምን ትለኝ?
እንደ «እብድ» ነው አይደል የምታየኝ?
ወይስ
እንደ ->ኔ አንተም
«ሞኝ! ሞኝ! - ነህ! ሞኝ!» ትለኝ?
ይሄ - ነው አየህ ችግሩ!
የ«ማን? - ምን?»
የ«ኔነት» ምን? ምንጭ ስሩ
መ - መ - ስ - ጣ - ጠ - ሩ ነው
ምስጢሩ!
እና....
ከሞኝም «ሞኝ» ከጅልም «ጅላ - ጅል»
«ዕብድ» ብትለኝ
ብታየኝ - አየሁህ
ባይህ - አየሽኝ
ሣምኩህ - ሣምከኝ
እንጂ
እኔን ከቶም አላወከኝ
እየው - አየህ? - እየው!
«ጉንጨን» - በ «ጉንጭ» ህ - ስትስለው
ካራዬ «ጀርባ»ህ ነው ያለው
እናም፡-

«ሞኝ» ካልከኝ «ሞኝ» ነህ
«ዕብድ› ካልከኝም «ዕብድ» ነህ
የሆንከውን ሁሉ ሆኜ
ባለህበት የምገኝ
«አንተ» ማለት «እኔ» ነኝ
«አንተ» ና «እኔ» - «አንተ»
«እኔ» ና «አንተ» - «እኔ» አንድ ነን
«አንተ» በኔ «እኔ» ባንተ እንኳ ነን።

# ዕርግማን!

ከደምሽ «ደሙ»
ከሥጋሽ «ሥጋው»
ተሠርቶ
ከሕይወትሽ - ሕይወቱ
ከማንነትሽ - ምንነቱ
ከስምሽ - «ስሙ»
ተጠርቶ
የጉያሽን - ትንፋሽ ለብሶ
ከመዳፍሽ - ከእጅሽ - ጉርሶ
ከማጀትሽ - ማዕድ - ቆርሶ
በእሹሩሩ ማሙሽ ልጄ!
በጀርባሽ ላይ ተመንድጎ!
ከእናትነት አንጀት ፍቅርሽ
የደም ጡትሽን ወተት ምጎ!
ለወግ! - ለማዕረግ!
ደርሶ
በውስጡ - ለውስጡ
ነግሶ!
መልሶ.....
ውለታሽን ከመመኘት

ለክብርሽ ከመቆም ፊንታ
ከአንቺነትሽ ፍቅር ባሻገር
ላበለጠው ከተፈታ
ሕሊናው ለሽፍጥ ከተረታ
በወንዝሽ የጥም - ዕርካታው
አዕምሮው «ከፉ» ከአሰላ
በመስከሽ የአካል መፈንጫው
እጁ ለበደል ካደላ
«አበስኩ - ገበርኩ!» እናንተ!
አቤት! የመኖር
አቤት! የማየት የመስማት ዕዳ!
የቀን የዘመን ፍዳ!
አይጣል ነው እንጂ አይጣል
ከዚህ ሌላ ምን ይወጣል?
ግና፡ - ብድሩ ይግባው
እንደ ከዳሽ - ይከዳ
ፍዳሽ ይሁነው ፍዳ
ልምድሽ - ይታጠፍበት
ጡትሽ «ቁሙ»ን ይውቀሰው
ዕንባሽ የእሳት ጐርፍ ሆኖ
አካል ገላውን ይግመሰው
እንዳሣዘነሽ ሲያዝን ይኑር

እንዳስከፋሽ ይከፋ!
በልፋትሽ እሱ ይልፋ!
ኑሮ ውሉ ይጥፋበት
ባሰበሽ ሃሣብ ይታሰብ
እንዳልሆነሽ «ሁሉ» አይሁነው
ስቃይ ለእርሱ ይሰባሰብ
ለንጋትሽ የጐህ ጀንበር
ለምትሽ ኮከብ ጨረቃ
አፅሙ ለከርሰ ምድርሽ
ለአፈርሽ ወግ አይብቃ!
ብኩን - ይሁን
ወዞ ይንጣ
በኖረበት ፈቀሬታ
በሄደበት አመኔታ
አንደበቱ ጣዕም ይጣ!
ስንኩል ይሁን ድኩማን
ዕርግማን!!

# የልቤ - ልብ

ከ«ልቤ»ም - በላይ ለ«ልብ» ሀ
የልቤ «ልብ» - ስልህ
እንዴት አዘንኩ ተድደቼ
እንዳረባኸኝ - ሰምቼ
ማን - ነገረህ ጃል?
እንዳትል - ምን ይበጅሃል?
ያጃጅልሃል!
እርግጥ -
-ባያስደስትህ
ባያሳዝንህ
-ባያስቅህ
አያስለቅስህ
ግና
ሣታውቅ ማወቄ ይከፋሃል።
ማወቄን - ካወቅህ ይረባሃል!!

# ባይፈትኑኝ

ቋንቋዬ - ላይሆን ቋንቋቸው
ዕውነቴ - ላይሆን ሸፍጣቸው
ብራብ - እንጂ ላይራቡ
ጥማቴንም ላይጠሙ
የሚታየኝ - ላይታያቸው
የሚሰማኝን ላይሰሙ
የቸገረኝ - ላይቸግራቸው
የቸገራቸው ላይቸግረኝ
ቅዠታቸው - ላያቃዠኝ
ምሬታቸው ላይበግረኝ
ምናለ - አቦ ቢተውኝ?
በነገር - ስለት ባይፈልጡኝ?
በዕልህ - እሳት ባያቀልጡኝ
ጽናቴን - ከቶም ላይንዱት
ዕውነቴን - ከቶም ላይረቱት
ቢያደሙኝ - እንጂ - ቢገድሉኝ
ኢትዮጵያ!
ከክብርሽ - ሞት!
ከፍቅርሽ መቼም ላይለዩኝ
አቦ - ምናለ ቢተውኝ

በመከራ ጽልመታቸው
        በማልወድቀው ባይፈትኑኝ?

# እስቲ - ይሁና!

«ተፈጥሮ» በርሱ ሲጨከን
«በደል»ም እርሱን ሲያመክን
ሁሉ - ነገር ለእርሱ ሲመር
ይባሱኑ በእርሱ ሲከር
ሲያዝን ሲተክዝ፥ ነገር በሆዱ ሲገባ
የ«ብሶት» እንባ - ሲያነባ
አንገቱን ወደ ሕዋው
        ወደ ሰማይ ያቀናና
መዳፎቹን ለዕለት ጀንበር
        ወይ - ለምሽት ያሰጣና
እንባዎቹን - ይረጭና
«እ - ህህ!» ይላል
«በረጅ - ሙ» ይተነፍሳል
የሆዱን ዕሳት ቃጠሎ
        ዕምቅ፥ እንፋሎት ሲያወጣ
ቃል ሲያጥረው፤ ሲቃ ሲያንቀው

የሚለውን ነገር ሲያጣ

ከዚያም መለስ እንደገና

ያስብና!- ያስብና!

ፍዝ - ዝ....ትክ - ዝ

ዓይኑን ቡዝ -ዝ ያደርግና

ከራስ ሙግት ይይዝና

«ቅን» አንገቱን ስብር አ'ርጐ

ወደ መሬት ይደፋና

በሀሣብ ቅኝት ሃሣብ ቋጥሮ

ስንጥር ቢጤ ሰነጣጥሮ

አፈር - ወዲያ! አፈር - ወዲህ

ምናምኑን ነገር ጭሮ

የእርሱን ብሶት ለእርሱ ነግሮ

‹ይሁና!....ይሁና!.....እስቲ ይሁና!

ሌላማ ከቶ ምን እላለሁ?

‹ሃቅ!› ምስክር ዳኛ ሁና

ቅን «ብይኗን» ከርሷ እሻላለሁ

እስቲ ይሁና!...ይሁና!

ሌላማ መቼስ ምን ይደረጋል?

«ጊዜ» የሚዳኝ በ‹ጊዜ› ነው

ለ«ሁሉም - ጊዜ አለው» ይላል

ይኸው ነው በቃ!

ያንዳንድ ሰው

የራስ ቋንቋ!

የዕብሪተኞች «እኩይ» ተግባር

ማንነቱን ሲያጨልመው

የዕውነትን የጉዞ ድር

ቀጭን መንገድ ሲያቀጭጨው

ሲያዝን ሲተክዝ፣

በሰው ምሬት ሰው ሲጨንቀው

ማድረግ ሳይቻል

አቅም ሲያንሰው

«ድብን -ን!» ሲል «ጭስስ!» ሲል

ብሶት «ክፉ» ሲያባብሰው

«እስቲ - ይሁና! ይሁና - ነው»

በ«ይሁን!» ነው የሚርሰው

-አንዳንድ ሰው።

በቃ! ከዚህ ሌላ

ምንም የለው

መከፋቱን መገፋቱን

የ«ጠዋት» ነው የሚመስለው

ያስከፋውን - አያስከፋ!

የገፋውን - አያስገፋ!

ዝም! ዝም! - በቃ - ዝም!

«ዝም - አይነቅዝም» ዓይነት
አንዳችም ነገር አይልም።
ምኑንም ለማን አይነግርም።
መፈጠሩን እንጂ የሚረግም።
ምንም - ነገር
አይናገር - አይጋገር
አይሞቅ፡ - አይበርድ
አይወታ፡ - አይወርድ
እንዲሁ፡ - ብቻ እንዲሁ
«እስቲ - ይሁና!» ሲል
በ«ይሁና» ልዕል ሲስል
በዕምቅታው ነው የሚከስል
እርሱ ለበደል «ዕጣ»
«በደል» ም፣ ለርሱ የተፈጠረ ይመስል።
ምንም ይቅር
ምንም ይምጣ!
በታች ይሁን
በላይ ጣጣ!
ፍቅር ይሁን
ወይም ቁጣ!
«እስቲ - ይሁና!
ይሁና! ነው» እንዳነሰው

አንዳንድ - ሰው።

# ማን ይሰለፍ?

ሀገር ስትጠቃ - ሀገር ስትደፈር
ሀገር ስትጣራ - ሀገር ስትል ሀገር
ከሥጋዋ ቁራጭ - ከማኅፀኗ ፍሬ
ለእናት ከልጅ ወዲያ - ማን ይመጣል ዛሬ?
ሀገር ስትቆስል - ሀገር ስትደማ
ድረሱልኝ ስትል - ጥሪ ስታሰማ
የጭንቋ ቀን ደራሽ - አለሁኝ የሚላት
ካለኔ በስተቀር ማን - ይምጣ ለኔ እናት
የአንድነት ጽናቴን - ነፃነት መርጬ
ለክብሬ ማን ይቁም - እኔ ተቀምጬ?
እኔ ልሁን እንጂ - የሀገር ምድር ትቢያ
አይደፍርሽም ጠላት - ኩሪብኝ ኢትዮጵያ
ማን ይጠብቅ ነፃነቴን?
ማን ያስከብር አንድነቱን?
ለማን ሀገር ማን ይሰለፍ?
ከኔ ሌላ ማን ይሰየፍ?

# ክፍል ሦስት

## ቅምሻ!

የ«አበው»ን

ተምሣሌት -

የስነ - ቃል፤ ውበት - ጥቅሻ

ለ«ቅምሻ!»

## ነገርን - ባጭሩ

ሀ - ባሉ

ተዝካር - በሉ

*******

ጭምት - ሲሞት

ልቡን

ትልቅ - ሲሞት

ግንቡን

*******

ከማይናገር - ከብቱን

ከማይራገጥ - ወተቱን

*********

በበላህ - ገብር

በሰማህ - መስከር

አንቱ - ትተረጉሙ

አንቱ - ትደረግሙ

**********

ዝባድን - ከውሻ

ዕምነትን - ከባለጌ አትሻ

********

ምስክር - ቢያድር

ይለወጣል

ሽንፍላ - ቢያድር

ይመለጣል

******

ብትጠላ - ብትወድ

ፍየል - መንታ ትወልድ

አንዱ - ለመጣፍ

አንዱ - ለወናፍ

********

## መናቅ

ተይ - መጭ!
ተይ - መጭ!
በቅሎዬ - ተይ - መጭ!
ነገር ካልሰሙት አይቆጭም!
*********

## ተረብ

ምን ተሸከመሃል?
የስንደዶ ፍልጥ
በምን አስረህ?
በወይራ ልጥ
ማን አሸከመህ?
ዝሆን ተካቦ
እንዴት ልታወርድ?
በትንም ደቦ
ስምህ ማን ይባል?
ላገር አይመች
ማን አወጣልህ?
ጐረቤቶች
እናትህ ማን ነች?
ሳትወልደኝ ሞተች።
********

## ለ - ጥጋብ ዘመን

እህል ዱር አዳረ
ብቻውንም ዋለ
ጠላት እንደሌለው
ሰው እንዳልገደለ
********

## ለ - ፍቅር

ዓይንሽን - ዓይና
ጥርስሽን - አይና
ክዳው ክዳው አለኝ
ያባትሽን - ዝምድና
እራሷን - ሹሩባ
ተሠርታው ብትመታ
ዓይኗን - በቀጭኑ
ተኩላው ብትመጣ
ጥርሷን - ጉራማይሌ
ተነቅሳው ብትመጣ
ሣልታመም ታመምኩ
ሣልሞት ነፍሴ ወጣ
*******

## ማሽኮርመም

እሺም አላለችኝ
እምቢም አላለችኝ
እንደ - ጠመጅ ቆሎ
ስቃ ዝም አለችኝ
አውራ ዶሮ ጭሮ
ስጥሺን ሲያፈሰው
እንዴት እሺ ማለት
ያስቸግራል ለሰው
********

## ለ - ማድነቅ

ይኸው ደረትሽ ነው፥
ያጣላው ሰውን
እስቲ ሸፋን አርጊው
ያጡት እንደሆን
*********

## ለ - ወንድ አደር

ዓይንሽ የብር ዋጋ
ጥርስሽ የብር ዋጋ
ወዳጆችሽ ብዙ ከስንቱ ልዋጋ?
******

## ለ - ቅናት

አንቺም ወዲያ ወዲያ፥
ወደ ሳበው ልብሽ
እኔም ወዲህ ሆኜ፣
ሰው አገኘሁብሽ
******

## በ - ስውር

ብድር ተበዳሪ -
ባለ ዕዳሽ አያርገኝ
ቀን አትሰጪም አሉ -
የቸገረው ቢገኝ።
ይሻላታል ብዬ -
ገዳም ባስገባት
«ያዝ - ረድ» እያሉ
አባባሱባት።
ፈረስ፥ በቅሎ - ጭኖ -
ከሚከተለው
እቤቱ ያለውን -
ይወደዋል ሰው።
ጥጡን ነድፈሽ ነድፈሽ -
ባልጋ ቆለሻል
ይህም አመል ምለሽ -
ብተይ ይሻልሻል።

*******

## ለ - ምልጃ

እማ - ሆይ!
ማርያም ስልሽ
ሃሣብ ትካዜዬን
ልነግርሽ
እንዴት? ወዴት?
አገኝሽ?
ይታደገን - ዘንድ
ልጅሽ!
*******

## ለ - ነገረኛ

ኩታ ለማሠራት
ጥጥ ገዛሁኝና
በኖ በኖ አለቀ
ነዳፊው በዛና
ነዳፊ ከበዛ፥
እኔም ጥመን ልግዛ
ነድፎ ነድፎ መፍተል፥
ከሆነ የዋዛ።

## ለ - ራስ ወዳድነት

ስጥ - ለኔ
ድገም - ለኔ
ስጥ ለእንግዳ
-አንተም ጠጣ
ለኔም አምጣ።
********

## ሀገርን - ለማዳን

ወግጂልኝ ድጓ -
ወግጂልኝ ቅኔ
ወንዶች ከዋሉበት
እውላለሁ እኔ።
***********

## ለ - ቁጮት

ሰሪ ፍጥረቱን አታለለ
በኖራ ሰራሁ እያለ
መች ይፈርስ
መች ይሰበር
ዕውነት ኖራ በነበር
********

## ሳለ - መጨቆን

ሞት ይቅር ያላሉ -
        ሞት ቢቀር አልወድም
ከድንጋይ - ቋጥኙ -
        ከሰው ፊት አይከብድም።
ማጣት ከፉ ከፉ፤
ችግር ከፉ ከፉ፤
        ተብሎ ይወራል
ከባርነት ቀንበር -
        ከሬት መች ይመራል።

## ለ - ጅገና

ተው! ተመለስ በሉት
ተው! ተመለስ በሉት!
        ያንን መጥፎ በሬ
ከጠመደ አይፈታም ያገሬ ገበሬ።
        ********
ያባቴ ነው ብሎ፤
የናቴ ነው ብሎ፤
        ይፋጃል በርበሬ
አባት የሌለው ልጅ፤
እናት የሌለው ልጅ፤
        አይሆንም ወይ አውሬ።
        ********

## ለ - ማስቆጣት

ኸረ ምረር ምረር

ኸረ ምረር ምረር

ምረር እንደ - «ቅል»

ስላልኮ - መጠጠ

ስላልመረረ ነው «ዱባ» እሚቀቀል።

# ስለደራሲው በጥቂቱ

የደራሲው ሥራዎች

1. የኔ ጋሻ (**ግጥምና ቅኔ**)
2. አንድ ቀን (**ግጥምና ቅኔ**)

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

"... በ—ግዚሀር
እንተ—እግዚሀር

አንድ ነገር ልጠይቅህ
እና—ንገረኝ
ሳትደብቀኝ ...
......

ከድርሻዬ
የ'ወር' ዓመት ደርሷል ዕድሜዬ
ከማንም ምንም ሳልሻ
ወደዚያ ወደዚህ ሳልዞር
የኖርኩትን ያህል ኖሬ
ያልኖርኩትን ግማሽ ለመኖር
ንገረኝ
ስንት ዓመት ነው የሚቀረኝ!..."

ማኅበረሰቡን ... ነው ።

"ሽበት ያሀል" ተብሎ ትመን የሚደዉማሉትን ያው ትንሽ ከምችት ማለዶት ከቅጥ ወደ ቅጥ በሙሩስ በማለቱ ሳለፍ ለትማና ትውልድ እንደበት እያቀበለ ነው ።

"እንደበት" ያልኩት አለብል ሃቅ አይደለም ። ሥነ ቃላትን ፣ የሚፈስገውን ያሀል ተሰባስቦ በወረቀት ክብር ውስጥ ያልመመ ዝገቡን ለመግለጥ ነው ።

ገጣሚ ክፍሌ አቦቸር ግን በዚህ የግጥሞች መድበል መጽሐፍ ውስጥ በዘለር ሰዎች ላይ የተጣለውን ሕዝባዊ አደራ በጥቂቱም ቢሆን የቀረፈው ይመስላል።

ውብ ፣ የተመረጠና የተከሸነ ሕዝባዊ ግጥሞችንና ፣ አባባሎችን ከነሰፃቸው ጣዕም ነበንሰባቸውና አጣፍጤትቸው አቅርቦልናል ። በዘይቤ የታገለ፣ ከውስጥ እኔነት ተጸንሰው የተወለዱ ወጥ የሆኑ ግጥም ውጤቶችም በጥናኔት የነበ

D AMH Kef
Kefle Abocar
Ande qan 1989
ihvu 1
03010255593001

ብርሃንና ሰላም ማ/ቤት ታተመ

ዋጋ ብር 3·00